**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ/መ/ቁ. 175483

መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች**፡- አቶ ሀቢብ ጀማል

**ተጠሪ**፡- አቶ ጀማል አሊ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ቼክን የሚመለከት ሲሆን ክርከሩ የጀመረውም በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች ላለባቸው እዳ ቁጥሩ CC3263602 የሆነ ቼክ በቀን 30/01/2009 ዓ.ም የሰጡኝ ቢሆንም ቼኩ ለክፍያ ሲቀርብ አመልካች ክፍያውን በማስቆማቸው ክፍያ ሊፈፀም አልቻለም፡፡ በመሆኑም በቼኩ ላይ የተመለከተውን ብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን ብር) ከጥቅምት 28 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ እና ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው የተጠሪ ምንም እዳ የሌለብኝ ሲሆን ቼኩ የተሰጠው ተጠሪ በስራ አስኪያጅነት በሚመሩት ድርጅትና እኔ በስራ አስኪያጅነት በምመራው ሌላ ድርጅት በጋራ የሽርክና ማህበር ፈጥረን ንብረትነቱ የመንግስት የነበረውን አርቲስቲክ ማተሚያ ቤትን በጨረታ ለመግዛት በመስማማታችን ሲሆን በጨረታውም ካሸነፍን በኋላ መንግስት ግራ ቀኛችን የመሠረትነውን

የሽርክና ማህበር አስተካክለንና በንግድ መዝገብ አስመዝግበን በጨረታው ያሸነፍንበት ቅድመ ክፍያ ብር 115,110,955.40 ካልከፈልን እርምጃ እንደሚወሰድ ሲያሳውቅ ተጠሪ ይህንን ገንዘብ በሁለት ቀን ውስጥ መክፈል አልችልም፤ ስለሆነም ለጨረታው ያስያዝነው ገንዘብ ከሚወረስ እኔ ከግዢው ልውጣና አንት ግዛው የሚል ጥያቄ አቅርበውልኝ ተስማምተን ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲሸጥና እንዲለውጥ ውክልና ለልጄ በመስጠት በቃለ-ጉባኤ የሽርክና ማህበሩን ስያሜ አስተካክለንና በንግድ መዝገብ አስመዝግበን ከድርጅቴ ብር 117,000,000.00 ወጪ በማድረግ ለማተሚያ ቤቱ ግዢ ክፍያ ፈፅሜያለሁ፡፡ ሆኖም ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ መብት ያላቸው በማስመሰል ከአመልካች ጋር ፀብ በመፍጠራቸው የጋራ ጓደኞቻችን በሽምግልና ተሰባስበው ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ አለኝ የሚሉትን መብትና ጥቅም እንዲተው እኔ ደግሞ በብር 1.8 ሚሊዮን እና በብር 2,000.000.00 (ሁለት ሚሊዮን) የሚመነዘሩ ሁለት ቼኮችን ለመስጠት ተስማምቼ ቼኮቹ ወጪ ተደርገው ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተጠሪ ባለ 1.8 ሚሊዮን ብሩን ቼክ መንዝረው ገንዘቡን ከወሰዱም በኋላ ስምምነታቸውን አፍርሰው ውክልናም አልሰጥም በማለታቸው የሁለተኛው ቼክ ክፍያ ሊታገድ ችሏል፡፡ አመልካች ለድርጅቱ ግዢ ብቻዬን ክፍያ ፈፅሜ እና ተጠሪ ስምምነታችንን አፍርሰው እያለ ቼኩ የሚመነዘርበትም ሆነ የተባለውን ገንዘብ የምከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የሰማው የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቼክ ለከሳሽ የሰጡት በጋራ ከመሠረቱት የሽርክና ማህበር እንዲወጡ ተስማምተው በመሆኑና ተጠሪ ቼኩን ከተቀበሉ በኋላ በሽርክና ማህበሩ ውስጥ መብትና ጥቅም አለኝ የሚል ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ ተጠሪ የፈፀሙትን ስምምነት በማፍረሳቸው አመልካች በቼኩ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ወይም ተጠሪ ዳኝነት ለጠየቁበት ጉዳይ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ጳጉሜ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በግራ ቀኙ መካከል በሽማግሌዎች የተላለፈው ውሳኔ ተጠሪ ማተሚያ ቤቱ ላይ ያለኝን መብት ትቻለሁ ያላሉ ሲሆን ስምምነቱ በግልጽ የሚለው የአመልካች ድርጅት በግራ ቀኙ የተመሠረተው የሽርክና ማህበር ምክንያት የሚመጣ ጥቅምም ሆነ ጉዳት ሓላፊነቱን የአመልካች ድርጅት እንዲወስድና ከተገኘው 11.5 ሚሊዮን ብር ውስጥ ለተጠሪ አመልካች በሁለት የተለያዩ ጊዜያት የሚመነዘር ቼክ ለመስጠት መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተስማምተዋል እንኳ ቢባል አመልካች ስምምነቱ ስለመጣሱ አላስረዱም፡፡ ከዚህ ባለፈም በንግድ ህጉ ቼክ ሀተታ የሌለበት እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ እንደሆነ፣ በአውጭውና በተቀባዩ ግንኙነት ላይ በተመሰረቱት አፃፃፍ ፎርምና ቃሎች ካልሆነ በስተቀር መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል ስለተደነገገ አመልካች በቼኩ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ሚያዝያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ 04 ገፅ የሰበር አቤቱታ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች ዘርዝረው በማቅረብ እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ ቼኩ ለተጠሪ የተሰጠው ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ ለመውጣት መስማማታቸው ሆኖ እያለ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህንን ስምምነት ከቼኩ ጋር አብሮ ማየት ሲገባው አለማየቱ፤ ጳጉሜን 1 ቀን 2008 ዓ.ም በሽማግሌዎች አማካኝነት በፈፀምነው ስምምነት ከሽርክና ማህበሩ የሚገኘውን ጥቅምም ሆነ ጉዳት መቶ በመቶ የአመልካች ድርጅት እንዲቀበል ተስማምተን ባለበትና ያስማሙን ሰዎችም ቀርበው ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ ያላቸውን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓለማ የገለግልም!

መብትና ጥቅም ለመተው መስማማታቸውን መስክረው እያለ የስምምነት ሰነዱ ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ ለመውጣት መስማማታቸውን አያሳይም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ቼኩ ለተጠሪ የተሰጣቸው ጳጉሜ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በሽማግሌዎች አማካይነት በስምምነቱ መሠረት ከሽርክና ማህበሩ መብትና ጥቅም ላለመጠየቅ የገቡትን ስምምነት በመጣሳቸዉ አመልካች ቼኩን ማሳገዳቸው ከንግድ ህጉ እና ካቀረቧቸው ማስረጃዎች አንፃር ተገቢነት የለውም የመባሉ አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ 05 ገፅ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሱ ይዘት በአጭሩ በሽማግሌዎች ፊት የተፈፀመው ስምነነት ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ ለመውጣት መስማማታቸውን አያሳይም፡፡ ስምነነቱ ወደ ሽርክና ማህበሩ ያለምንም ድካም የሚገባ ሌላ ሰው ተገኝቶ ያለምንም ድካም በመግባቱና ገንዘቡን አመልካች በመረከባቸው ለአራት ሰዎች መከፋፈሉን ነው የሚያሳየው፡፡ ተጠሪ በግላቸው የሽርክና ማህበሩ አባል ስላልሆኑ ከማህበሩ ሊወጡ የሚስማሙበትና በዚህም ምክንያት የሁለት ሚሊዮን ብር ቼክ የሚቀበሉበት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ሊፀና ገባዋል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአመልካች ክርክር ቼኩን ለተጠሪ ፈርሜ አልሰጠሁም ወይም ክፍያው እንዳይፈጸም አላሳገድኩም የሚል ሳይሆን፣ ቼኩ የተሰጠው ግራ ቀኝ በሚመሯቸዉ ሁለት ድርጅቶች የሽርክና ህብረት ፈጥረዉ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅትን ለመግዛት ተስማምተዉ የዋጋዉን ቅድመ ክፍያ ተጠሪ መክፈል ባለመቻሉ አመልካች የተጠሪን ጭምር እንዲከፍል እና ተጠሪ ከግዥዉ ዉስጥ እንዲወጣ በተስማሙት መሠረት ገንዘቡ በአመልካች ተከፍሎ ማተሚያ ቤቱ ከተገዛ በኋላ ተጠሪ ስምምነቱን ወደ ጎን በመተዉ በድርጅቱ ዉስጥ መብት ያላቸዉ በማስመሰላቸዉ በሁለቱ መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ በሽምግልና ተሰባስበዉ አመልካች ለተጠሪ 3.8 ሚሊዮን ብር እንዲከፍሉ፣ ተጠሪ ደግሞ ከህብረት ሽርክና ማህበሩ መብትና ጥቅም አለኝ ላይሉ ተስማምተዉ በዚህም መሠረት ቼኩን ከተቀበሉ በኋላ 1.8 ሚሊዮን ብር የተጻፈበትን ቼክ መንዝረው ገንዘቡን ከወሰዱ በኋላ በድርጅቱ ውስጥ መብት እንዳላቸው በማስመሠል አመልካች የማደርገውን ሂደት በማሰናከላቸው ለዚህ ክርክር መነሻ በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ እንዳይከፈል ያገዱ መሆኑን ነዉ፡፡

በመሠረቱ ቼክ እንደ ገንዘብ በቀላሉ ወደተለያዩ ሰዎች ሊተላለፍ የሚችል ባህርይ ያለዉ የሐዋላ ሰነድ ነዉ፡፡ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘ እና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል ስለመሆኑ እንዲሁም በቼክ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ ለአምጪዉ ያልተከፈለ እንደሆነ አዉጪዉ ለቼኩ አከፋፈል ኃላፊነት እንዳለበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 827(ሀ)፣ 854፣ 640 እና 868 ስር የተመለከተዉም በዚሁ መሠረተ-ሃሳብ መነሻነት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸዉ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ ስለሆነም ቼክ አዉጪዉ ቼኩ ለተሰጠዉ ሰዉ ክፍያዉ አይገባዉም በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የሚኖረዉ ህጉ ለይቶ

በአንቀጽ 717 ስር ካስቀመጣቸዉ ሁኔታዎች አንዱን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ነዉ፡፡ በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ በቼክ ሰጪዉ እና በቼክ አዉጪዉ መካከል የግል ግንኙነት መኖር ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 24435 (በቅጽ 12 ላይ እንደታተመዉ) እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ቼክ ካለዉ ልዩ ባህርይ የተነሳ ተገቢዉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አዉጪዉ ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ ከአምጪዉ ጋር የነበራቸዉ የግል ግንኙነት መኖሩን በመቃወሚያነት አቅርቦ ሊከራከር ይችላል ማለት ነዉ፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ አመልካች በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ እንዳይከፈል ሊያግድ የቻለዉ ተጠሪ በሽማግሌዎች ፊት በተደረገዉ ስምምነት መሠረት የገቡትን ግዴታ በመጣሳቸዉ ምክንያት ነዉ በማለት ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩላቸዉ የጣሱት ስምምነት አለመኖሩንና አመልካች ቼኩን ለተጠሪ የሰጠዉ ተጠሪ ከድርጅቱ እንዲወጡ ሳይሆን ለድካም ዋጋ መሆኑንና ተጠሪ የቅድመ ክፍያ ለመክፈል የአቅም ችግር እንደሌለባቸዉም በመጥቀስ ይከራከራሉ፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባ መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት በጭብጥነት ተይዞ መጣራት የሚገባዉ ነጥብ አመልካች ቼኩን ለተጠሪ የሰጡት ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ ያላቸዉን መብትና ጥቅም እንዲተዉ በተደረገዉ ስምምነት መሠረት መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡ ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ቼክ ካለዉ ልዩ ባህርይ የተነሳ በላዩ ላይ የተመለከተዉ ክፍያ በፍርድ ኃይል እንዲከፈለዉ በቼክ አዉጪዉ ወይም በጀርባ ፈራሚዉ ላይ ክስ የሚያቀርብ ሰዉ ከቼኩ ዉጪ ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይጠበቅበትም፡፡ ይልቁንም ተከሳሽ በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ ለከሳሹ ሊከፈል አይገባም የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ የተከራከረ እንደሆነ ይህንኑ ምክንያቱን አስቀድሞ የማስረዳት ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም አከራካሪዉ ቼክ ለተጠሪ የተሰጠዉ ከላይ በተገለጸዉ መልኩ በግራ ቀኞቻቸዉ በተደረገ ስምምነት ምክንያት መሆኑን የማስረዳቱ ሸክም የአመልካች ሲሆን፣ አመልካች በክርክሩ መሠረት አስረድቷል ወይ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ነዉ፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ኃላፊነት የለበትም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ቼክ አመልካች ለተጠሪ ሊሰጡ የቻሉት የመንግስት የልማት ድርጅት የነበረዉን አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅትን በጨረታ ተወዳድሮ ለመግዛት ተጠሪ በዋና ስራ አስኪያጅነት የሚመሩት ኮርፖሬት ኮምፒዉተር ማዕከል የተባለዉ ድርጅት እና አመልካች በዋና ስራ አስኪያጅነት የሚመሩት ፈለቅ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሽርክና ፈጥረዉ ጨረታዉን ካሸነፉ በኂላ ተጠሪ ወይም ድርጅታቸዉ የሚጠበቅባቸዉን የቅድመ ክፍያ ሊያገኙ ባለመቻላቸዉ አመልካች የተጠሪን ድርሻ ጭምር ቅድመ ክፍያ መክፈላቸዉን እና ተጠሪ ብር 3.8 ሚሊዮን ከአመልካች ወስደዉ ከግንኙነቱ እንዲወጡ ከስምምነት መድረሳቸዉን እና በዚህም መሠረት ተጠሪ 1.8 ሚሊዮን ብር ከወሰዱ በኂላ በዚሁ ምክንያት የተሰጣቸዉና ለዚህ ክርክር መነሻ በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ብር 2 ሚሊዮን ከመመንዘሩ በፊት ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ መብትና ጥቅም አለኝ የሚል ጥያቄ በማንሳት ከማተሚያ ድርጅቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ዉሎች ለአመልካች እንዲጨርስ ለልጃቸዉ ሰጥተዉ የነበረዉንም ዉክልና በማንሳታቸዉ ምክንያት አመልካች በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ እንዳይከፈል ማገዳቸዉ ተረጋግጧል በማለት ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ አመልካች በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ሲወስን በመሠረታዊነት የጠቀሰዉ

ምክንያት ተጠሪ መብቱን ለመተዉ መስማማቱን የሚያሳይ ማስረጃ ካለመቅረቡም በላይ ተስማምተዋል እንኳ ቢባል ተጠሪ ስምምነቱን ማፍረሱ አልተረጋገጠም የሚል ነዉ፡፡

በበኩላችን እንደተመለከትነዉ፣ አመልካች ክርክሬን ያስረዳልኛል ያላቸዉን የተለያዩ የሰነድ እና የሰዉ ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ አንዱ ጳጉሜ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በሽማግሌዎች ተሰጠ የተባለን ዉሳኔ የሚያሳይ ሰነድ ነዉ፡፡ ሰነዱ በሰበር አጣሪ ችሎት ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይህ ሰነድ “የተወሰኑ የሽማግሌ ዉሳኔዎች” የሚል ርዕስ የተሰጠዉ ሲሆን፣ የስድስት ሽማግሌዎች እንዲሁም አመልካች እና ተጠሪን ጨምሮ ሦስት ሰዎች “የባለጉዳዮች ፊርማ” የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በሰነዱ ላይ ፈርመዋል፡፡ ይህ ሰነድ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቼክ ለተጠሪ የተሰጣቸዉ ምንም ዓይነት መብትና ጥቅም ከሽርክና ማህበሩ ላለመጠየቅ ግዴታ በመግባት ባደረጉት ስምምነት መሠረት መሆን ያለመሆኑን በአግባቡ ለመረዳት እንዲቻል የሰነዱ ይዘት እንደሚከተለዉ ተመልክቷል፡-

## <u>ዉሳኔ</u>

የተነሱትን ነጥቦች በማየት የሚከተሉትን ዉሳኔ ወስነናል፡፡

1ኛ. በህብረት ሽርክና ምክንያት የሚመጣ ተጠያቂነትን በተመለከተ፡- ፊለቅ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በቀጣይም ከዛሬ ጀምሮ ለሚኖር ጥቅምም ይሁን ጉዳት ለሚመጣ ነገር 100% ኃላፊነት መዉሰዱን የሚያረጋጥ ዋስትና በደብዳቤ እንዲሰጥ ለኮርፖሬት ኮምፒዉተር ማዕከል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ወስነናል፡፡ ደብዳቤዉም በዉልና ማስረጃ እንዲጸድቅ ይህም በሐሙስ ጳጉሜ 03 2008 ዓ.ም በአቶ ጀማል እንዲሰጥ፡፡

2ኛ. የተገኘዉን 11.5 ሚሊዮን ብር መከፋፈል በተመለከተ

ሀ. ለሐጂ ሽኩር አህመድ 2 ሚሊዮን ብር እንዲከፍል ቀሪዉን ለሐቢብ ጀማል 40% ለጀማል አሊ 40% እና ለሐይደር ከማል 10% እንዲከፋፈሉ ወስነዋል.፡፡

ለ. የአከፋፈል ሁኔታ በሚል ርዕስ ለተጠሪ እና ለአቶ ሐይደር ከማል የተሰጡትን የቼክ ቁጥር ይጠቅሳል፡፡

ከዚህም የምንረዳዉ ሰነዱ የሽማግሌዎች ዉሳኔ እንጂ አመልካች እንደሚለዉ ስምምነት ካለመሆኑም በላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቼክ የተሰጠዉ ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም ላለማንሳት ወይም ለመተዉ ግዴታ ገብተዉ በመስማማታቸዉ ምክንያት መሆኑን አያሳይም፡፡ በመሆኑም የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህን ሰነድ በዋቢነት በመጥቀስ ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ ተጠሪ ከሽርክና ማህበሩ ያላቸዉን መብትና ጥቅም ለመተዉ ግዴታ በመግባታዉ ነዉ በሚል የደረሰበት ድምዳሜ የሰነዱን ትክክለኛ ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የጽሑፍ ሰነድ በላዩ ላይ ስለሚገኘዉ የስምምነት ቃል

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርዮ አረደደ ምዓለማአ የገለግልም!

በተፈራራሚዎች መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ መሆኑን እና በዉሉ ዉስጥ ስለተፃፉት ቃላቶች የሰዉ ምስክር ወይም የህሊና ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል እንደማይቻልም የፍትሐብሔር ህጋችን አንቀጽ 2005(1) እና 2006(2) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ ተጠሪ ከማህበሩ ያላቸዉን ድርሻ ለመተዉ በመስማማታቸዉ ምክንያት ስለመሆኑ አላስረዱም እንጂ፣ አስረድቷል ቢባል እንኳ በሰነድ ማስረጃዉ ላይ በግልጽ ያልተመለከተዉ ይዘት በሰዉ ምስክሮች ሊረጋገጥ የሚችል ባለመሆኑ የምስክርሮቹ ቃል የተያዘዉን ጭብጥ የማስረዳት ህጋዊ ብቃት የለዉም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቼክ ለተጠሪ መስጠቱን ሳይክድ በመካከላቸዉ በሽምግልና በተደረገዉ ስምምነት መሠረት ተጠሪ የገቡትን ግዴታ በማፍረሳቸዉ ቼኩ እንዳይመነዘር ማገዳቸዉን ገልጸዉ የተከራከሩ ቢሆንም ይህን ክርክራቸዉን የሚያስረዳ ማስረጃ ግን አላቀረቡም፡፡ አመልካች ለክርክራቸዉ መሠረት ባደረጉት መልኩ በመካከላቸዉ ስምምነት መኖሩ ካልተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ ስምምነት የጣሱ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ በሁለተኛነት የተያዘዉን ጭብጥ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ  አመልካች ለቼኩ መዉጣት ምክንያቱ ተጠሪ የሽርክና ማህበርን ድርሻ ለመተዉ በመስማማታቸዉ ምክንያት መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 162460 በቀን 11/07/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጸጸምዓለማአ የገ ለግልም!

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!